ዓለም አቀፍ የአማራ ኅብረት
11303 Amherst Avenue, Suite 2
Silver Spring MD, 20902

ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደሬሽን ምክር ቤት
ለተከበሩ አፈ ጉባኤ አቶ አደም ፋራህ
አዲስ አበባ

ቀን ነሃሴ ፪፫ ፳፻፩፪

ጉዳዩ ፥ በህወሓት ፖለቲካዊ ሴራ ምክንያት በወልቃይትና የራያ አማራ ህዝቦች ላይ ስለተደቀነ የተራዘመ ግፍና የማንነት ጭፍለቃን ስለመከላከል

ባለፈው የስላሳ ዓመታት ሀገሪቱ የገባችበት የፖለቲካ ቀውስ የመራው የህወሓት ድርጅት አርጅቶና ተዳክሞ ከስልጣን ቢሰናበትም ካለፈዉ ሁለት ዓመታት ወዲህ የሥርዓቱ ቀንደኛ አራማጆች የነበሩት ወደ መቀሌ በመሸሽና የትግራይን ህዝብ ምሽግ በማድረግ በተጨማሪም አጎራባች ህዝቦችን በማጋጨት ወደተባረሩበት ሥልጣን የሚመለሱበትን ሴራ ሲያቀነባበሩ እንደቆዩ መረዳት አያዳግትም። ትህነግ በ1991 ሃገሪቱን ሲቆጣጠር አማራ-ጠል የህገመንግስታዊ ፕሮግራምና ሰፊዉን የአማራ ህዝብ የጽንፈኞች ተጠቂ የሚያደርግ ርእዮተዓለም በመዘርጋት በተለይ የወልቃይትና የራያ ህዝቦችን በግፍ ህይወታቸውን በማጥፋትና በአካባቢዉ መጠነሰፊ የኢኮኖሚ አሻጥር ሲፈጽም መቆየቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ህወሓት የወልቃይትና የራያ ህዝቦችን ያለማቋረጥ በማስፈራራትና በማፈን ወይንም በማባረርና በመግደል የራሱን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ መሰረት ለመትከል እንዲያስችለው በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የነዚህን ማህበረሰብ አባላት በማጎሪያ እስር ቤቶች ጭምር በማፈንና በማጥፋት የአማራ ትውልድ ምን ጊዜም ቢሆን ሊረሳው የማይችል ሰቆቃና ግፍ እንደሆነ እያንዳንዱ የፌደሬሽን ምክር ቤት አባላት የሚረዳው ጉዳይ እንደሆነ እናምናለን። በህወሓትና አጋሮቹ ተቀነባብሮ እስከ አሁን ስራ ላይ ዉሎ በሃገሪቱ ሰፍኖ ያለዉ፤ ብሔርን መሠረት ያደረገ ሕገ-መንግሥት ያስከተለዉን ሃገር አቀፍ ምስቅልቅል በገሃድ የምናየው ሃቅ ከመሆኑም በላይ በተከታታይ የተከተለው ፖሊሲና ስራዎች፤ የስርዓቱን እድሜ ለማራዘም በሚያስችል ደረጃ ብቻ፤ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር የማጋጨት ተንኮሎች መፍጠርና ስኬታማ ማድረግ፤ ብዙ ሚሊየን ሕዝብ ከቀየው እንዲወገድ አስገድዶ ኢትዮጵያዊያንን ከጎንደር ወልቃይት--ጠገዴ ከጋምቤላ እስከ አፋር፤ ከኦሞ ሸለቆ፤ ከኦጋዴን ከጎጃም ቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ እስከ መተማ፣ ከወሎ ራያን ከአዲስ አበባ ፤ ከኦጋዴን ከተማና በመላው ትግራይ በያሉበት ማፈንና ማሰቃየት፤ በእድገት ስም የገጠርንና የከተማ መሬቶችን ወረራ በማድረግ ለጥቂት የህወሓት/ኢህአዴግ አባላት፤ ደጋፊዎችና ኢንቬስተሮች ማዘዋወር፤ ነዋሪዎች አቤቱታ ሲያቀርቡ በተገላቢጦሽ እነሱን ሕገ መንግሥቱን

አላከበራችሁም፤“ሽብርተኞች ናችሁ” በሚሉ ሰበቦች ወንጅሎ ማሰርና ማሰቃየት የተለመዱ ስልቶች ሆነዋል። በአጠቃላይ ስርአቱ ሕገ መንግሥታዊ እውቅና ሰጥቶ ተግባራዊ ባደረገው ብሄርን መሰረት ያደረገ የክልሎች አሸናሸንና በተለይም ጎልቶ በሚታየው፤ በወልቃይት ጠገዴን የራያን፤ የሰብአዊ መብቶች አፈና፤ በነዋሪዎች ላይ በተከታታይና በተቀነባበረ መልክ በህወሓት መሪነትና ቀስቃሽነት በገዢው ፓርቲ በተካሄደው ግፍ፤ እልቂትና የመሬት ነጠቃ ዙሪያ ነው።

ህወሓት ከ1991 ጀምሮ የወልቃይትና የራያ አማራ ለም መሬቶችን በመውረር ለማካለል የወሰደው እርምጃ ተፋፍሞና ቀጥሎ በዚህ በተጠነሰሰው የምርጫ ፖለቲካ የሚያስከትለው መንግስታዊ ያለመረጋጋት የሃገሪቱን ሰላም በቋሚነት ለማደፈርስ መሆኑን በመረዳት የወልቃይትና የራያ አማራ ህዝቦች ሮሮ በጥልቀት ተመልክቶ እነዚህን ህዝቦች ከትህነግ የጭፍለቃ ድራማ መታደግ የፌደሬሽን ምክር ቤት በሃገሪቱ የፌደራል መንግስታዊ ስርዓት የመቀጠል ዋስትና አድርጎ ሊያየው እንደሚገባ እናሳስባለን። ወልቃይት ጠገዴ አማርኛም፣ ትግርኛም ሆነ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትጵያውያን የሚኖሩበት በታ ሲሆን ከህወሀት/ ኢህአዴግ ስርዓት በፊት በነበሩት ያስተዳደር ጊዜያት ውስጥ ማለትም በደርግ፣ በቀዳማዊ ሀይለስላሴ፣ በአጼ ምኒልክ፣ በአጼ ዩሐንስ መንግሥታት የሚተዳደረው በትግራይ ፣ በኤርትራ ወይም በሌላ ሳይሆን በበጌምድር/ በጎንደር ቀደም ሲልም ባካባቢው አስተዳደሮች ስር እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ። እንዲሁም በተመሳሳይ ረገድ ራያ የወሎ ክፍለ ሀገር አካል እንደሆነ የቅርብ ታሪካችን መሆኑን ዐለም አቀፍ የአማራ ኅብረት ይኼን የታሪክ ሂደት ይቀበላል።የወልቃይት ጠገዴንና የራያን ህዝብ ለመስረታዊ መብቱ መከበር፣ የሚካሄድበትን የመሬት ነጠቃ መፈናቀልና ሌሎችንም የግፍ ተግባሮች አጥብቀን እናወግዛለን። ለዚህም የመብት ትግል ያለውን ድጋፍና ከህዝብ ጎን መቆሙንም ዐለም አቀፍ የአማራ ኅብረት ያረጋግጣል።

ኢትዮጵያውያንን እርስ በርስ የሚያጋጭና የሀገርን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል የመሬት ነጠቃና ስፊ ከፋፋይ ፖሊሲ እቅድ አውጥቶ ስኬታማ ለማድረግ ችሏል። ብዙ ክፍለ ሀገራትን አዲስ አበባን ጨምሮ ለኦሮሞ ክልል በሎ ሲያስረከብ፣ ለራሱም ህወሃት የወልቃይት ጸገዴን ፀለምትና የራያ ለምልም መሬቶችን አፋርን ጨምሮ ለራሱ ጠቅልሎ ወሯል፤ በነጠቃቸውና እንደፈለገ በሸነሸናቸው መሬቶች የሚኖረውን ሕዝብ አፍኗል፤ አስሯል፤ በአንዳንድ ቦታዎች፤ ለምሳሌ በወልቃይት-ጠገዴ ዜጎችን ጨፍጭፏል፤ እንዲሰወሩና እንዲሰደዱ አድርጓል።

በዚህ አጋጣሚ በ2010 ዓ,ም በሃገሪቱ የመንግስታዊ አስተዳደር ለውጥ እንዲቀሰቀስና እንዲቀጣጠል ያስቻሉ ያማራ ወጣቶች ያማራ መስተዳደር አባላት እንዲሁም መላው የሃገሪቱ ህዝብ የተጫወተዉን ሚና ለማስታወስ እንወዳለን።ይሁንና አዲስ የለውጥ አመራር አለ ከተባለ ጀምሮ በአማራ ህዝብ ላይ በህወሓት የተጫነ የግፍና መከራ ቀንበርን ለማቅለል የተሞከረ የፖለቲካም ሆነ የፍትህ እርምጃዎች እንዳልተተገበሩ ይታያል።በተለይ በአሁኑ ሰዓት ህወሓት ያለብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ህጋዊ ፈቃድና ዕውቅና በተለይም የተወካዮች ምክር ቤትን ምክንያታዊ የምርጫ ማራዘሚያ ድንጋጌ በመናቅ እንዲሁም የፌደሬሽን ምክር ቤቱን በጉዳዩ ላይ ያለዉን ህግና ስልጣን ከምንም ባለመቁጠር በምንይዘው የሳምንት መጨረሻ የትግራይ ክልላዊ ምርጫ ሰበብ በማድረግ መንግስታዊ አስተዳደርን፣ የሃገሪቱን ሰላምና አንድነት በሚያናጋ መልኩ በማናለብኝነት ሃይልን አደራጅቶና በተቀነባበረ ስልት ወደ ነበረበት አገዛዝ ለመመለስ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

የአለም አቀፍ አማራ ህብረት ይህንን ህወሓት የፈፀመዉን መጠነ ሰፊ የሰበዊ መብት ጥሰት በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ምርመራ እንዲደካሄድ ተገቢ ጥረት እያደረገ ሲሆን የፌደሬሽን ምክር ቤቱ ፣ የተወካዮች ምክር ቤትና የመከላከያ ሰራዊት በዚህ በቀጥዩ ሳምንት እነዚህን የአማራ ሰቆቃ ወረዳዎች ገንጥሎ ሀገር ለመመስረት እየሞከረ ያለው ትህነግ በቸልታ በመመልከት በታሪክ ተወቃሽና ተጠያቂ

ከሚያደርግ ስህተት ይልቅ  የትህነግ ሴራን በአስቸኳይ በቁርጠኝነት የሚመከት አቋም እንዲኖረው በጥብቅ ማሳሰብ እንወዳለን።
ዐለም አቀፍ የአማራ ኅብረት የአሁኑ የቋንቋ/ብሄር "ከፋፍለህ ግዛው" ስርዓት አገር አፍራሽ፤ የመሬት ወረራን ጸረ- ሰላም፤ ጸረ- ፍትህ-ርትህ፤ ጸረ-ሕዝብና ጸረ-ዲሞክራሲ ስለሆነ፤ ስርዓቱ ተወግዶ እውነተኛ ሕዝብን የሚወክል፤ ለሕዝብ ተገዢና ታዛዢ የሆነ ስርዓትና መንግሥት እንዲመሰረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ የሚያደርገውን ትግል ከመቸውም በበለጠ ደረጃ ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ እናስታውቃለን።
ዐለም አቀፍ የአማራ ኅብረት በተለይም በትግራይ ክልላዊ መንግሥት በቅርቡ በሚካሄደው ምርጫ ከአማራ ክልል በጉልበት/ በፖለቲካ ውሳኔ ወደትግራይ በተጠቃለሉት መሬቶች ላይ በሚኖሩት የአማራ ተወላጆችና የእርስቱ ህጋዊ ባለቤቶች ላይ እየደረሰ ያለውን ግድያ እስራትና ማፈናቀል አጥብቀን እናወግዛለን::

በተለይም የወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ሁመራና የራያ ህዝቦች የማንነትና የዜግነት ጥያቄአቸው ባልተመለሰበት ሁኔታ ለትግራይ የሪፈረንደም ምርጫ በሚመስል መልኩ በእነዚህ ሕዝቦች ላይ እየደረሰ ያለው መከራና ወከባ እጅግ በጣም ልብ የሚሰብር ክስተት ሆኖ አግኝተነዋል::

## በጳጉሜ በሚደረገው ክልላዊ ምርጫ ካልተሳተፉ አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ ታዘዋል

እኛ የዓለም አቀፍ የአማራ ኅብረት አባላት የፌደሬሽን ምክር ቤትንም ሆነ የኢትዮጵያን መንግስት የጉዳዩን አሳሳቢነትና የሚያስከትለውን መዘዝ በጥሞና ተመልክቶ እነዚህን ግፉዓን ባስቸኳይ እንዲታደጋቸው ነው:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ በግዴታ ምርጫው ተካሂዶና ማንነታቸው በግፍ ተጨፍልቆ የትግራይ ሪፈረንደም ማስፈጸሚያ እንዲሆኑ በግፍና በህገ ወጥ መንገድ ወደትግራይ ቢጠቃለሉ ይኸን ምርጫ ተከትሎ የሚመጣውን ማንኛውንም ውጤት የአማራ ህዝብ እንደማይቀበለው በአጽንኦት እናረጋግጣለን:: በውስጥም በውጭም የሚመለከታቸውን ለማሳወቅ አስፈላጊውን መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ ነን:: ስለሆነም የኢፌድሪ ምክር ቤትና የኢትዮጵያ መንግሥት የሚከተሉትን ውሳኔዎች እንዲአስተላልፍልን በትህትና እንጠይቃለን::

ሀ) የፌደራል መንግሥት  ለእነዚህ ህዝቦች አስፈላጊውን ጥበቃና እንክብካቤ እንዲአደርግላቸው

ለ) የማንነታቸው የዜግነታቸው በኃል ተጨፍልቆ ባለበት ሁኔታ በምርጫው እንዳይሳተፉ እንዲደረግ

ሐ) የማንነትና የወሰን ጥያቄ በአግባቡ እስኪመለስ ድረስ  ከህወሓት የጭቆና አገዛዝ ተላቀው በፌደራል መንግሥት ስር እንዲቆዩ እንዲደረግ

መ) ይህ ሳይሆን ቀርቶ በማስፈራራትና በድፍጠጣ ምርጫው ቢደረግ  ምንም ዐይነት ዕውቅና ሳይሰጥ ውጤቱ ውድቅ እንዲደረግ
ሠ) በእነዚህ በእብሪተኝነት በተወሰዱ መሬቶች ላይ በሚኖሩ ህዝቦች ላይ እየተደረገ ያለው ግድያ እስራትና  መፈናቀል  በህግ  አልያም  በኃይል እንዲቆም አጥብቀን እንጠይቃለን

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

አምባቸው ወርቃ (ዶ/ር)
የአለም ዓቀፍ አማራ ህብረት ሊቀ መንበር

ግልባጭ

ለተከበሩ ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዓብይ አህመድ
ለተከበሩ ለኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ደመቀ መኮንን አዲስ አበባ
ለተከበሩ ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ
ለተከበሩ ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንት ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ
ለተከበሩ ለአማራ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳደር አቶ ተመስገን ጥሩነህ
ባሕርዳር
ለተከበሩ አፈ ጉባኤ ሩፋኤል ሽፈረ ሱባ ብሄራዊ ክልል ትግራይ
ለተከበሩ ወይዘሪት ብርቱካን መደቅሳ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
ለተከበሩ በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባስደር አቶ ፍጹም አረጋ
ዋሽንግተን ዲሲ
ለተከበሩ ለሰብአዊ መብት ጉባኤ አቶ ቢኒያም አባተ አዲስ አበባ
ለተከበሩ ኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ማኅበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ያሬድ ኃይለማርያም
ብረሰልስና ጄኔቫ